# ሰሞኑን በፓል ቶክ

ከቤልጂግ አሊ

ንፅህ ኢትዮጵያዊ የሚለውን ፅሁፍ ከአቀረብኩ በሆላ አንዳንድ ነገሮች ስለሚያስደንቁኝ፣ሆነ ስለሚገርሙኝ ወደ ፓል ቶክ የሱስ ያህል ማዘውተሬ አልቀረም ። በዚህ ሳምንት ከሁሉም በላይ „የንፁህ ኢትዮጵያዊንት „ ሹመት በደደቦች ሽንጎ ያለገኘው ኢሕአፓ እራሱ ነው ። ባለፊው ዶክተር ታዬን ከበደው በዚህ ሳምንት ህብረቱንና ኢሕአፓን ። ነገ ደግሞ ማን እንደሚቀጥል መገመት ይቻል ይሆናል ።

ይህንን ሹመት አትስጡን ከናንተ አንፈልግም ሊባል ነው ።ለመስጠት ትችላላችሁ ወይ ተብሎም መጠየቁ አይቀርም ። አጋፋሪዎቹን ስመለከታቸው የፖለቲካ ችሎታቸውን ጥያቄ ውስጥ ለመክተት ያስስበኛል።ብዙ ልምድ ስላለን ልንጠነቅቅበትም ይገባል። ነፍሱን አይማረው እና ካለ መደህኒያለም የደርግ ስርአት ፣ ለእልቂቱ የተጠቀመው የቦዘኔውን ክፍል አስታጥቆ እንደነበር የሚታወስ ነው ። ከዛ በመነሳት ዛሬ በየፓልቶኩ ቀኑን ሙሉ ሲሳደብ የሚውለውን ሰው ግላዊ ባህሪ አዲስ የተመሰረቱ ድረርጀቶች ሊያጠኑት ይገባል እላለሁ ። አለበለዚያ ግን የሚመጣው ችግር ዛሬ „ በቆሻሻዎቹ ኢትዮጵያውያን „ ላይ ከስድብ ባያልፍም፣ይሁን እንጂ ነገ የራስን ድርጅት እንደሚያፍረከርክ አልጠራጠርም ።ያ ቤልጀግ ምን አለ በሉ በውጭ ያለን ቅራኔን በቅጥ መያዝ ካልተቻለ በውስጥ የሚነሳውን ቅራኔ መቆጣጠር አይቻልም ። ይህ ካልሆነ እያንዳንዱ አጋፋሪ የየራሱን ደብር ይዞ ሲዋጋ ነው የሚውል ።

አሁን ያለውን ሁኔታ ስንመለከተው አዲስ በተፈጠሩት ድርጅቶች መካከል ባለው የስልጣን አለመረጋጋት ምክንያት አንዱ ክፍል ሌላውን ሊያጠቃበት የሚችለው መንገድ ስለሆነ ከድርጅት አሰራር ባሻገር ነፃ ሰጥቶ እሱም የተወካይነት ጥያቄውን አሸንፎ ሊወጣ የሚችልበት መንገድ ነውና በሁኔታው ሲደሰት ይታያል። ሆኖም ሁኔታዎች ሲረጋጉ ትንቢት ተናጋሪው አትበሉን እንጂ ድርጅት መከፋፈልንም ያመጣል ።

ለአፈ ግም አፍንጫ ድፍን ያዝለታል እንዲሉ የሚሰደቡት ቆራጥ ታጋዪች ይህን ከመጤፍ ሊቆጥሩት አይገባም ። እኛ ግን እንደህዝብ በግለሰብ ደረጃ በየቦታው እየተገኘን የወያኔንና የሻቢያን አንቀላፊዎች ተነቅቶባችሆልና ተመልሳችሁ ተኙ ማለት ያሻል ። እንዳንዱን የፓልቶክ አጋፋሪ እኔ በበኩሌ የስድሰተኛ ክፍል የሚኒስተሪ ወረቀቱ ቢጠየቅም አይከፋም እላለሁ ። ወይም እንግሊዘኛውን እንዲተው መምከር ያስፈልጋል ።እናንተ እንደኔ ደርሶባችሁ ይሆን አላውቀም አንዳንድ ግዜ በአማርኛው መገባባት እየከበደኝ አንግሊዘኛው ሲጨመርበት ይበልጥ እያደኛገረን መጥቶአል ።እንደው የሚኒስተሪ ወረቀት ይጠየቅ አልኩ እንጂ ስንት ፌዞ ዶክተር እንዳለ አጥቼውም አደለም ። እንዳንዴማ ከስራ ጡረታ ከወጡ በሆላ እውቀቱ የሚጠፋባቸው አይጠፉም።

ለቀልድ ያህል አመጣሁት እንጂ የኢሕአፓን የሰላሳ አምስት አመት ታሪክ በደደቦች ሸንጎ ሲሰለቅ መስማት ምን ያህል የሚዘገንን መሆኑን አጥቼው አደለም ። የስንት ቆራጥ ታጋዮች ስም የአባቱን ብለቅ ደደብ ያርገኝ ብሎ በተነሳ ደደብ አገፋሪ ሲጠፋ ማየት እንዴት ይዘገንናል። ምን ያህልስ ጨካኝነት ነው ሙትን መውቀስ ። ምን ያህልስ ከሃዲነት ነው አገርን መሸጥ ከዛም ብሎ ሽያጩን አፅድቁልን ማለት ።

እዚህ ላይ ቢነበብ ይጠቅማል ብዬ የማሰበው መፀሀፍ አለ እሱም „ **The Wave by Morton Ruhe** „ ነው ። ከዛ በሆላ ነው የኔ ችግር የሚገባችሁ ። ዛሬ ልንቆጣጠረው ያልቻልነውን ነገ ሊያመጣ የሚችለውን ጥፋት መቆጣጠርም አንችልም ። አሊያ የሚመጣው መፈክር የተለመደው „ዴሞን በዴሞፈተር“ ብች ነው ።

በዚህ ሳምንት በፓል ቶክ ያየሁትም ይህንኑ ነው ።ሁሉም ለእየራሱ አርቲ ነው ፈሱ እንዲሉ፤ አፃፈው በሌሎች ሲመለስ የሚያመጣው የወያኔን እድሜ መስንበት ነው ።ይህ ከሆነ ታድያ ህብረትን እነፈልጋለን የሚሉ አመራሮች ገደብ ያጣውን ስድብ ሊያስቆሙት ይገባል ። አለዚያ ግን የመደራደሪያ መድረካችን ነው ብለው የሚያስቡም ከሆነ ሌሎቹ ተቃዋሚዎች በዚህ ስነስርአት ባጣ መንገድ ሰለማይደራደሩላቸው ካሁኑ ቢያቆሙት ሳይሻል አይቀርም ።

የዚህ ሳምንቱ ፓልቶክ እዚህ ላይ ላቁመና ለሚቀጥለው ሳምንት ማነህ ባለ ተራ የኪዳነ ምህረት ወዳጄ ያስጠመቅህ ባሰራስድስት ፤ ለመሰደብ ብዬ ላቁም ።

ቤልጀግ አሊ ።